# ከአረጀ፡አይበጁ።





ክቡራትና፡ክቡራን፡- በዚህ፡ቀውጢ፡የአረመኔ፡አምባገነኖች፡ዘመን፡ትኩረታችንን፡በአረመኔው፡ለገሠ፡ዜናዊ፡አስተዳደር፡ላይ፡በማድረግ፡ፈንታ፤የሕዝብን፡እንቅስቃሴ፡አቅጣጫ፡ለማስለወጥ፡በሚጥሩ፡መምህር፡መስፍን፡ወልደ፡ማርያም፡አወናባጅ፡አገላለጽ፡ታውከን፣ለህዝብ፡እሮሯችንን፡እንድናቀርብ፡መገደዳችን፡አሳዝኖናል።

ሆኖም፣መስፍን፡ወልደ፡ማርያም፡የመልክዓ፡ምድር፡መምህር፡እንጂ፡የሥነ፡መንግሥት፡ፈሊጥን፡በሕዝባዊ፡አገዛዝ፡ሁኔታ፡ሊያሳኩ፡የማይችሉ፡መሆናቸውን፡አስመስክረዋል።አስተዳደጋቸው፡የትግሬ፡ጉዲፈቻ፡መሆኑ፡እና፡የወላጅ፡ቤተ፡ሰብ፡ፍቅር፡ሳያዩ፡በማደጋቸው፡ዐመፀኛነት፡ያመታባቸዋል።ለሀገር፡እና፡ሕዝብ፡ቁልፍ፡ዐዋቂዎችን፡በመበጥበጥ፡እና፡በማስረሸን፡የታወቁ፡ናቸው።ለዋቢነትም፣ደርግ፡ለፍርድ፡ተቸግሮ፡አማካሪ፡ቢያደርጋቸው፡"ፈረሱም፡ይኸው፣ሜዳውም፡ይኸው፡ምን፡ትጠብቃላችሁ"።ብለው፡ኢትዮጵያን፡በቅን፡ያገለገሉት፡ዕውቅ፡ምሁራን፡እና፡ሹማምንት፡ማስረሸናቸው፡ታሪክ፡ይቅርታ፡የማይለው፡ነው።

መስፍን፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ለክፉ፡ቀን፡እና፡ለወደፊት፡ሀገርን፡አልሚ፡ይሆኑናሉ፡ብሎ፡ግብር፡ከፍሎ፡ካሳደጋቸው፡ወላጅ፡አልባ፡ተማሪዎች፡አንደኛው፡ናቸው።ተቀማጥለው፡በአዳሪ፡ትምህርት፡ቤት፡ስለ፡መማራቸውም፡የሰውነት፡ማጐልመሻው፡ዕውቅ፡መምህር፡ክቡር፡አቶ፡ግርማ፡ቸሩ፡ሰሞኑን፡በኢሳት፡ነፋስ፡ምሥል፡እና፡ድምፅ፡ቃለ፡መጠይቅ፡በአቶ፡ሲሳይ፡አጌና፡ቀርቦላቸው፡በተከታታይ፡የመለሱትን፡ጎዋ፡ሰሌዳ፡ወይም፡ፊት፡ገጽ፡ውስጥ፡መመልከቱ፡ጠቃሚ፡ነው።

"ሰው፡ሲታጣ፣ይመለመላል፡ጐባጣ"።ሆነና፡ሰሞኑን፡ስለ፡ክቡር፡አቶ፡ከበደ፡ሚካኤል፡መስፍን፡የጻፉትን፡............"የፋሺስቱ፡ኢጣልያ፡አገልጋይ፡የነበሩት፡ከበደ፡ሚካኤል፡በታሪክና፡ምሳሌ፡ውስጥ፡አንዱን፡ጣሊያን፡ሲያነጋግሩት፡-

"ኃይለኛ፡እየሄደ፡ያስገብራል፡የትም፣

መሬት፡የሁሉ፡ናት፡ባለቤት፡የላትም።ብለውለት፡ነበር።"ብለው፡ቁም፡ለቁም፡ተርጉመው፡ወጣቱን፡ትውልድ፡ለማወናበድ፡የከጀሉት፡መስፍን፡ወልደ፡ማርያም፡ሰምና፡ወርቁን፡ለይተው፡ምሥጢሩንም፡አውጥተው፡ለማስረዳት፡ተስኗቸዋል።ይኸን፡ለተተኪው፡ትውልድ፡ግራ፡አጋቢ፡መልእክት፡ሲያበረክቱ፡ተመልክተን፡እና፡ሰውየው፡በሕይወት፡ኖረው፡መልስ፡መመልስ፡አለመቻላቸውን፡ስናሥብ፡እጅግ፡በጣም፡ስለ፡ተሰማን፡ይኸን፡ልንጽፍ፡ተገድደናል።ለክቡር፡አቶ፡ከበደ፡ሚካኤል፡ሀገር፡እና፡ሕዝብ፡አገልግሎትም፡የውስጥ፡አርበኛ፡በመሆን፤ቀን፡እየሠሩ፡የጠላትን፡ሁኔታ፡በማጥናት፣ሌሊት፡መሣሪያ፡ይዘው፡ለጐደቡ፡አርበኞች፡ያዩትን፣የሰሙትን፣በመግለጽ፡እና፡ስንቅ፡ከአልባሳት፡ጋራ፡

በማቀበል፥ሥራ፥ባሻገር፤ምሥክርነት፥መጻሕፍቶቻቸውን፥ከቤተ፥መጻሕፍት፥ፈልጎ፥መመርመር፥ይበቃል።

የክቡር፥አቶ፥ከበደ፥ሚካኤል፥ግጥም፥ወይም፥ቅኔ፥ሰምና፥ወርቅ፥ያለው፥በመሆኑ፥ተለይቶ፥መቅረብ፥ነበረበት።ይኸን፥ካልን፥በኋላ፤ሰሙ፥- ኃይለኛ፥ወይም፥ጉልበተኛ፥በፈለገበት፥ሄዶ፥መሬት፥በመቀማት፥ያስገብራል።ለተከታዩ፥ጭፍራውም፥ያደላድላል፥ነው። ወርቁ፥ደሞ፥- ፩ኛ-መሬቱን፥የተቀማ፥ሁሉ፥በአልሰጥ፥ባይ፥ተከላካይነት፥ሲዋጉ፥በሁለቱም፥ወገን፥የሞተው፥የሚቀበሩበትን፥አመልካች፥አድርገው፥መሬት፥የሁሉም፥ናት፥አሉት። ፪ኛ-ሬ፥ጠብቆ፥እና፥ላልቶ፥መሬት፥ሲነበብ፥መራራነትን፤ቆምጫጫነትን፤ቁጡነትን፤አልበገር፥ብሎ፥መከፋትን፥ገላጭ፥ነው።እንጂ፤መስፍን፥ወልደ፥ማርያም፥እንዳሉት፥የከሃዲነት፥በነሱው፥ቋንቋ፥የባንዳነት፥ባሕርይ፥በክቡር፥አቶ፥ከበደ፥ሚካኤል፥ላይ፥አልነበረም።

መስፍን፥ወልደ፥ማርያም፥ሲጽፉ፥እና፥ሲናገሩ፥ከመቃወም፥በስተቀር፥ኃላፊነትን፥የሚፈሩ፥ናቸው።አሁንም፥በፍራቻ፥የአረመኔው፥ትግሬ፥ወያኔ፥አስተዳደርን፥የሚያበረታታ፥ሥራ፥በመሥራት፥ላይ፥ናቸው።ከድርጅቶች፥ጋራ፥በመተባበር፥ፈንታ፥እየገቡ፥ይከፋፍላሉ።የኢሰመጉ፥አሳቢ፥በመምሰል፥የጀመሩትንም፥ውጤተ፥ቢስ፥ሆኖ፥እናየዋለን።እንደ፥እርሳቸው፥በጉዲፈቻ፥ላደጉ፥ዛሬ፥ኢትዮጵያውያት፥እህቶቻችን፥እና፥ሕፃናት፥በጉዲፈቻ፥ሲቸበቸቡ፥በበለጠ፥ውስጥ፥ዐዋቂ፥ዋቢነት፥በመቆም፥ሸንጣቸውን፥ገትረው፥መሟገት፥ነበረባቸው።ግብር፥ከፍሎ፥ላስተማራቸው፥የኢትዮጵያ፥ሕዝብም፥ውለታ፥መክፈያቸው፥ጥሩ፥አጋጣሚ፥ሆኖላቸው፥ሳለለ፥ታሪክን፥እያጣመሙ፥ለሚጽፉ፥ትግሬ፥ወያኔ፥ወገኖቻቸው፥ሲያበረታቱ፥እናያለን፥እና፥የኢትዮጵያ፥ሕዝብ፥ተንኮላቸውን፥ዐውቆ፥እንዲጠነቀቅባቸው፥እናሳስባለን።

## ኢትዮጵያ፥እና፥ሕዝቧን፥እግዚአብሔር፥አጠንክሮ፥ይባርክ።አሜን።

# ኢትዮጵያ፥ለዘላለም፥ትኖራለች።

ከዜናማርቆስ፥መርሐ፤ካናዳ።
እ፥ጦማር፥- zienamarqos@yahoo.com